# ላለው ይጨመርለታል

አብርሃም በየነ

የሌለውን ትቶ ላለው ለመጨመር
ንፉግና ለጋስ የሆነውን እግዜር፤

ከደሙ ስጎነጭ ከስጋው ጎርሼ
እንደሰው ኖርኩና ሞቱን ተዋርሼ፤

እርቃኔን ስመለስ በወጣሁበት በር
መቼም ቅር አይሰኝ ብሄድ ያለማፈር።

# የብርሃን ፋይዳ

ለዕይታ ድህነት ላስተውሎት መኻን
ጨለማ እንዲመስል የፀሀይ ብርሃን፤

በዕውራን መሃከል ብርሃኑ በርቶ
ማጭበርበር ሲጀምር ጨረሩ ዐይን ወግቶ፤

አልከፈት ያለው ሲስለመለም ዐይኑ
መልቀቁን የማያይ ጨለማ ለቀኑ፤

ብርሃን የጎደለው የዐይነ-ስውር መንጋ
በደረቁ ሌሊት ነቅቶ ይላል ነጋ።

ታህሳስ 2004

---



EthioLion.Com